# <u>እ.ኤ.አ ከሜይ 21-31/2018 የነበረው</u>

# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>


በመጨረሻዎቹ የሜይ አሥራ አንድ ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠናከሩ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የዝናቡ ሁኔታ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ የተሻለ እንደ ነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። በመሆኑም በተለያዩ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ የተለያየ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከተፈጠረው ጠንካራ የደማና ክምችት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በአድዋ 48፣ በአይራ 36.2፣ 47.5፣ 45.0፣ 32.5 በአልጌ 50.0፣ 38.0፣ በአምቦ 41.5፣ በአርጆ 55.0 እና 36.4፣ በአዴት 41.4፣ በባህር ዳር 33.0፣ በበደሌ 35.4፣ በቤጊ 45.4፣ በብላቴ 66.7፤ በቻግኒ 72.8፣ በጎሬ 38.7፤ በጂንካ 48.5፤ በጎሎልቻ 34.1፤ በጨዋቃ 36.2፤ በቦሬ 35.1፣ በደሎመና 38.0፣ በኢጃጂ 39.5፣ 53.6፣ 38.7 በጊምቢ 45.1፣ በጅማ 34.9፣ በኮፈሌ 40.4፣ በኮንሶ 37.2፣ በምእራብ አባያ 31.6፤ በማንኩሽ 45.0፣ በባህር ዳር 33.0፣ በማሻ 31.7 እና 37.8፣ በሞያሌ 36.0፣ በነቀምቴ 50.9፣ በፓዌ 53.6፣ በወላይታ ሶዶ 38.6 እና 47.9፣ በሻውራ 41.0፣ በሲርባአባያ 55.8፣ በወሊሶ 35.1፣ በያቤሎ 41.4፣ በአክሱም 39.0፣ በአማን 41.4፣ በደብረ ታቦር 42.7፤ በዳንግላ 39.7፤ በዲላ 30.8፤ በላሬ 34.0፣ በማጂ 53.8፣ በአሶሳ 40.7፤ በጃራ 36.0 እና በቡርጂ 36.6፣ በሚ.ሜ. ይገኙበታል።

በአጠቃላይ ዝናቡ ከዕለት ወደ ዕለት በምዕራባዊው አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ነበረው። በዚህም መሠረት በትግራይ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ በምዕራብ አማራ እና በምዕራብ ኦሮሚያ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ዝናብ አግኝተዋል። በተጨማሪም በምሥራቅ አማራ፣ በመካከለኛውና በምሥራቅ ኦሮሚያ እና በደቡብ ሶማሌ ቆላማ ቦታዎች በጥቂት ቦታዎች ላይ ዝናብ ነበራቸው።


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበው ዝናብ ከቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ5-217 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ በመካከለኛውና በምዕራብ ትግራይ፤ ከአማራ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም እና ባህርዳር፤ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ በጋምቤላ፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች፤ በአብዛኛው ኦሮሚያ፣ ከሶማሌ ክልል በጅግጅጋ፣ በደገሀቡር፣ በፊቅና በቆራሄ ዞኖች፤ አዲስ አበባ እንዲሁም በድሬዳዋና በሀረሪ ከ2-11 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከ5 ሚ.ሜ. ያነሰ ዝናብ ከ 2 ላነሱ ቀናት ያህል አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2 )።

በአሥራ አንድ ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን በአማካይ ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በመካከለኛውና በምዕራብ ትግራይ፤ ከአማራ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ በጋምቤላ፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች፤ አብዛኛው ኦሮሚያ፤ ከሶማሌ የደገሀቡር፣ የፊቅና የቆራሄ ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የሆነ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ግን ከመደበኛው በታች ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ።


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2   ኢ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31 /2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




# እ.ኤ.አ ከሜይ 21-31/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የሜይ የመጨረሻዉ አሥራ አንድ ቀናት የበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተሻለ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ አብዛኛው የበልግ አብቃይና የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ቦታዎችን ያደረሰዉ እርጥበት ዘግይተውም ሆነ ቀደም ብለው ለተዘሩት የበልግ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራትና ለቀጣይ እድገት ጠቀሜታ ነበረው፡፡ እንዲሁም በመኸር ተጠቃሚ አካባቢዎች የተገኘዉ እርጥበት ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የማሳ ዝግጅትና ለዘር ስራ እንቅስቃሴ፣ ለቋሚ ሰብሎች የውሀ ፍላጎት መሟላትና ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ የነበረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ለአብዛኛው የእርሻ እንቅስቃሴ ጠቀሜታው የጎላ የነበረ ቢሆንም፤ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ አሉታዊ ጎን ነበረዉ፡፡ ከነዚህም ዉስጥ በብላቴና እና በቦሬ የነበረዉ ከፍተኛ ዝናብ በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ ሲሆን፤ በጉልልቻ በነበረዉ በረዶና ንፋስ የቀላቀለ ከፍተኛ ዝናብ በሰብሎችና በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡ በሌላ በኩል በምስራቅ አማራና በደቡብ ትግራይ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የእርጥበት መቀነስ የነበረ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ለበልግ ሰበሎች እድገት በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ጎን ነበረዉ (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4   እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከሜይ 21-31 /2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 21-31 ሜይ 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የነበራቸው አብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥሸለቆ፣ የገናሌዳዋ አዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች፣ ጥቂት የላይኛው ዋቢሸበሌ እና አዋሽ እንዲሁም አብዛኛው አባይና ጥቂት የመካከለኛው ተከዜ ተፋሰሶች ናቸው$ በሌላ በኩል መጠነኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች ደግሞ ጥቂት የገናሌዳዋና የአባይ ምስራቃዊው ክፍል፣ አብዛኛው ተከዜ፣ በጥቂት የላይኛው አዋሽ፣ በጥቂት የደቡብ ባሮአኮቦ፣ የስምጥሸለቆ አዋሳኝ ቦታዎችና የዋቢሸበሌ አዋሳኝ ተፋሰሶች ናቸው$ የተቀሩት አብዛኛው አፋርደናከል፣ የተከዜ ምስራቃዊው ክፍል፣ በጥቂት የአባይና የተከዜ ምስራቃዊው ክፍል፣ የመካከለኛውና የታችኛው አዋሽ፣ አብዛኛው ኦጋዴንና የታችኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተውሏል (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከጁን 1-10/2018 የሚኖረው
## የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ በጁን የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ የሀገሪቱን አካባቢዎች ጨምሮ ቀስ በቀስ የሰሜን ምዕራብ ክፍሎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው ።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ኢሉአባቦራ፣ አብዛኛዎቹ የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ እንዲሁም አርሲና ባሌ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ የሰሜንና የጎንደር ዞኖች፣ የባህር ዳር ዙሪያ፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብና የመካከለኛው ዞኖች፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ዞኖች በተጨማሪም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል አብዛኛው ዞኖች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና አልፎ አልፎም በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በጥቂት ሥፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊከሰት ይችላል። በአንጻሩ ከኦሮሚያ ቦረናና ጉጂ፤ ከሶማሌ ክልል የጅግጅጋ እና የሲቲ ዞኖች በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ አነስተኛ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ዞኖች ግን ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

## እ. ኤ. አ ከጁን 1-10/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ
## በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የጁን ወር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገራችን አካባቢዎች የመኸር ስራ እንቅስቃሴ ማለትም የማሳ ዝግጅና የተዘጋጁ ማሳዎችን በሰብል የመሸፈን ተግባራት በስፋት የሚስተዋልበት ሲሆን፣ በአንዳንድ የበልግ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች የበልግ ሰብል የሚደርስበትና በተወሰኑ ቦታዎችም የሰብል ስብሰባ ተግባራት በከፊል የሚከናወንበት ወቅት ነው፡፡

በተሰጠው የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት በተለይም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የዝናቡ ሁኔታ በመጠንም ሆነ በስርጭት ሊጠናከር እንደሚችል መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በአካባቢዎቹ ላይ እየተከናወነ ላለውም ሆነ ለሚጠበቀው የግብርና እንቅስቃሴ በአብዛኛው መልካም ጎን እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በትንበያው ላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚጠበቀው ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል አንፃርም ሆነ አስቀድመው የተዘሩና በተለያየ ዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግም ሆነ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ የቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሀ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

በአንፃሩ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በሚገኙ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት፣ የአረም መስፋፋት፣ እንዲሁም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ከአፈር መሸርሸርም ሆነ ከመሬት መንሸራተት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ሊያስከትል ስለሚችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነዉ፡፡ በተጨማሪም የሚጠበቀው ዝናብ የደረሱ የበልግ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድርግ በመካከል በሚገኙ ደረቅ ቀናት የሰብል ስብሰባ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል በተጠቀሱት የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው እርጥበት ምንም እንኳን በመጠን ዝቅተኛ ቢሆንም፤ በተለይም ባሳለፍናቸው ተከታታይ ቀናት አካባቢዎቹ ካገኙት የተሻለ እርጥበት ጋር ተዳምሮ የመጠጥ ውሀ አቅርቦትንም ሆነ የግጦሽ ሳር ልምላሜን እንዲሁም የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ ምንጮችን እንደሚያጎለብት ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ጋር ተያያይዞ የእንስሳት ልማት ላይ ጥሩ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡

## **እ.ኤ.አ ከጁን 1-10/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ**

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የክረምት ዝናብ መግባት ጋር ተያይዞ የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ በሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ በሚገኙ ተፋሰሶች የዝናቡ ስርጭትና መጠን የተሻለ እንደሚሆን ትንበያው ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም በመጪዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ የአባይ ተፋሰስ ምዕራባዊው አጋማሽ፣ የመካከለኛውና

የታችኛው ተከዜ፣ የመካከለኛውና የላይኛው አዋሽ፣ እንዲሁም የላይኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ መጠን ያለው ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ትንበያው ይጠቁሟል$ በተጨማሪም የመካከለኛው አዋሽና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች በጥቂት ቦታዎች ላይ አነስተኛ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል$ ከዚህ ጋር ተያየዞ የክረምቱ ዝናብ በመጀመሩ ለጎርፍ ተጋላጭነት ላላቸው ተፋሰሶች ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ይሆናል$